ግንቦት 23 ቀን 2009 ዓ.ም

# ማስታወቂያ

በሞንትሪያል (ካናዳ) በሚገኘው በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪየሽን ድርጅት (ICAO) ለኢትዮጵያ ተወካይ ጽ/ቤት በስራ ቀናት በጠዋት ሺፍት ብቻ የምትሰራ አንድ የጽ/ቤት ፀሐፊ (Administrative Assistant) በካናዳ ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን መካከል አወዳድሮ መቅጠር አስፈልጓል፡፡

ስለሆነም ለመወዳደር የምትፈልጉ ከዚህ በታች በሰፈሩት መስፈርቶች መሠረት መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

*<u>አስፈላጊ መስፈርቶችና የምዝገባ ሁኔታ፡-</u>*

1. አግባብነት ያለው ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ እና የስራ ልምድ
   - በጸሐፊነት ሙያና ቢሮ አስተዳደር ወይም በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የኮሌጅ ዲፕሎማ እና 4 ዓመት የስራ ልምድ ያላት፣
   - የኮምፒውተር ስልጠና ያላት፣
   - አማርኛ፣ እንግሊዘኛ እና ፈረንሳይኛ የመስማት፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ ያላት፣
2. የስራ ጊዜ ፡- በስራ ቀናት በጠዋት ሺፍት ለ4 ሰዓት፣
3. ደመወዝ፡- በስምምነት
4. ጾታ፡- ሴት
5. የምዝገባ ቦታ፡- ኦታዋ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ኤምባሲ
6. የስራ ቦታ፡- በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪየሽን ድርጅት (ICAO) ለኢትዮጵያ ተወካይ ጽ/ቤት-**ሞንትሪያል**

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች የምታሟሉ አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ከ ግንቦት 24 ቀን ጀምሮ ካሉት 5 ተከታታይ የስራ ቀናት በኋላ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ መረጃችሁን በመያዝ በአካል ኦታዋ በሚገኘው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ኤምባሲ ወይም መረጃችሁን በኤምባሲው ኢ-ሜል፡- info@ethioembassycanada.org ወይም በፖስታ በመላክ መመዝገብ ትችላላችሁ፡፡ ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 613-565-6637 ext 213 መደወል የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ኤምባሲ**

**<u>ኦታዋ</u>**